ቁጥር/Ref.No: ኢ.ሲ.ማ.ዓ.ም/ሴ7 204/15

ቀን/Date ሐምሌ 18/2015 ዓ.ም

## ከኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በወቅታዊ ጉዳይ ላይ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጀቶች ምክር ቤት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጀቶችን ለመወከልና ለማስተባባር በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት የተቋቋመ ነው። ምክ ር ቤቱ ይህን ተልዕኮ ለመወጣት መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በቅንጅት እና ትብብር በመስራት የዘርፉን ሁለንተናዊ ሀገራዊ አስተዋጾ ለማሳደግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። ከዚህ ጋር በተያያዘም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጀቶች ደህንነታቸው ተጠብቆና በነጻነት ተንቀሳቅሰው ስራቸውን እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃገራችን አንዳንድ አካባቢዎች በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት የሰብዓዊ ድጋፍ ሰራተኞች ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት ምክር ቤቱን በከፍተኛ ሁኔታ አሳስቦታል። በቅርቡም በአፋርና አማራ ክልል የተወሰኑ አካባቢዎች በስራ ላይ በነበሩ የሰብዓዊ ድጋፍ ሰራተኞች ላይ የሞት አደጋ መድረሱን ለማወቅ ችለናል። የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤትም የተፈጸመውን ድርጊት በጽኑ ያወግዛል። ምክር ቤቱ በተፈጠረው አሳዛኝ ክስተት የተሰማውን ጥልቅ ሐዘን እየገለጸ ለሟች ቤተሰቦች፤ ወዳጅ ዘመዶችና የስራ ባልደረቦች መጽናናትን ይመኛል፡፡

በተያያዘም ከቅርብ አመታት ወዲህ በሃገራችን በተለያዩ አካባቢዎች እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶች የዜጎችን ህይወት እየቀጠፉ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ አካላዊ ፤ ስነልቦናዊ እና ቁሳዊ ጉዳት እያደረሱ ይገኛሉ። በቅርቡም በጋምቤላ ብሔራዊ ክልልዊ መንግስት አንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ በጋምቤላ ወረዳ፤ በጎግ ወረዳ እና በጋምቤላ ከተማ የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ በንጹሃን ዜጎች ላይ የደረሰው ሞት፤ መፈናቀልና የሰብዓዊ ቀውስ እንዲሁም ከግጭቱ ጋር ተያይዞ በዜጎች ላይ የተፈጠረው የደህንነት ስጋት በእጅጉ ምክር ቤቱን ያሳስበዋል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት ተለዋዋጭ የግጭት ዓውድ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት እርብርብ፤ በተለይም የመንግስትን ልዩ ትኩረት የሚፈልግ የወቅቱ አሳሳቢ ጉዳይ እንደሆነ ምክር ቤቱ ይገነዘባል፡፡ እንደ ሐገር ለገጠመን የግጭት አዙሪት መቋጫ እና ዘላቂ መፍትሔ ማግኘት የሚቻለው ሁሉን አካታች በሆነ የሰላም እና የፖለቲካ ሂደቶች፤ ልዩነቶችን በውይይትና በሰለጠነ መንገድ ለመፍታት በሚደረጉ ጥረቶች ፤ የግጭት ምልክቶችንና አዝማሚያዎችን ቀድሞ በመለየትና ፈጣን ምላሽ በመስጠት ጠንካራ የግጭት መከላከል ስራዎችን በመስራት እንዲሁም አጥፊዎችን ተጠያቂ በማድረግ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በሚደረጉ ጥረቶች እንደሆነ ያምናል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ECSOC ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

(251) 11 853 2005/8/9
Email: ECSOC22@gmail.com
URL:www.ecsoc.net
@ethiopian.cso_council
@Eth_CSO_Council
@ethiopian_cso_council
Ethiopian Civil Society Organizations Council
Location: Left flank, 3rd floor, Hibr Building of Hibret Bank, Addis Ababa Ethiopia

Scanned with CamScanner

- ሁሉም በግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሰብዓዊ ድጋፍ ሰራተኞችን ደህንነት እንዲያከብሩ እና እንዲጠብቁ፤
- ሁሉም ባለድርሻ  አካላት በየአካባቢው ለሚስተዋሉ ግጭቶች መንስዔ እና የስር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ሰላማዊና  ዘላቂ በሆነ መንግድ እልባት እንዲያገኙ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡና እርብርብ እንዲያደርጉ፤
- አለመግባባቶችንና ልዩነቶችን በተከታታይ የውይይትና ድርድር አማራጭ መንገዶች  ለመፍታት ጥረቶች እንዲደረጉ፤ ያሉ በጎ ጅምሮችም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ
- መንግስትም የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት የማረጋገጥ ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ ጥሪውን እያቀረበ፤

ምክር ቤቱ  በሰላም ግንባታ ዙሪያ  የጀመራቸውን  ጥረቶችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል በድጋሚ ያረጋግጣል፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
ECSOC
ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

***ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት***

*የኢትዮጵያ  ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ገለልተኛ ተቋም ሲሆን የሲቪል ማህበረሰብ ዘርፉን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከ4600 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው፡፡*

CS Scanned with CamScanner